# በፀና መሠረት ላይ የቆ ህዝባዊ ሠራዊት

**አባ መላኩ** 03-16-17

የኢትዮጵያ ህዝቦች የዕድገት ተስፋ ከሠላም፣ ከልማትና ከዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ብቻ የሚመጣ ነው። እናም ለዘመናት የዜጎችን አንገት ያስደፋውን ድህነት አሸንፎ ለድል ለመብቃት እየተደረገ ባለው እልህ አስጨራሽ ትግል ውስጥ ትልቁ ፈተና ሊሆን የሚችለው የአካባቢያዊ ቀጣና ያለመረጋጋት ችግር መሆኑ አጠያያቂ አይደለም።

ለዚህ ደግሞ ከአጎራባች አገራት የሚመነጨው የሽብርተኝነት አደጋን መጥቀሱ ተገቢ ይሆናል። እርግጥም ይህ አደጋ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን፣ በክፍለ - አህጉሩ አካባቢ ለሚገኙ እንዲሁም ለሌሎች አገራት ጭምር ምን ያህል አስጊና አስከፊ እንደሆነ በተጨባጭ እያየን ያለነው እውነታ ነው።

ታዲያ እውነቱ ይህ ከሆነ ዘንዳ፤ የአጎራባቾቻችንን ሁኔታ ምን ጊዜም በትኩረት በመከታተል በአንድ በኩል በጎ ተጽዕኖዎችን ለማስፋፋትና ለማጎልበት፣ በሌላው በኩል ደግሞ ጎጂ ተፅዕኖዎችን ለመቀነስ ብሎም ለማስቀረት በጋራ እጅ ለእጅ ተያይዞን መረባረቡ የአማራጮች ሁሉ አማራጭ ነው። በቀጣናችን ካሉት አገሮች መካከል ጎረቤት አገር የሆነችው ሶማሊያ የአሸባሪዎች መፍለቂያና መናኸሪያ በመሆን ለአካባቢው አገራት በተለይም ለአገራችን ሥጋት ሆና መቆየቷ ከማንም የተሰወረ አይደለም።

ሁሉም እንደሚገነዘበው መንግሥት አልባ በነበረችው ሶማሊያ የመሸጉ የተለያዩ የጦር አበጋዞችና አሸባሪ አክራሪ ቡድኖች፣ የገዛ አገራቸውን ህዝብ ሠላምና መረጋጋት ከመንሳት አልፈው የቀጣናውን አገራት በሽብር የማመስ ዓላማን አንግበው ሲሯሯጡ ነበር። ለዚህም በተለያዩ ጊዜያት በአገራችንና በጎረቤት አገሮች ያደረሷቸው የሽብር ጥቃቶች ከበቂ በላይ ማሣያዎች ናቸው። በተለይም በአገራችን ላይ የጅሃድ ጦርነትን አውጀውብን እንደነበርም አይዘነጋም።

እርግጥ ሠላም ወዳዱ መንግሥታችን ከረጅም ጊዜ ትዕግስት በኋላ አገራችን ራሷን የመከላከል ርምጃ እንድትወስድ ማድረጉ፤ በወቅቱ ተደቅኖባት ከነበረው ግልፅና ድርስ አደጋ ሊታደጋት ችሏል።

ታዲያ እዚህ ላይ 'አገራችን በሶማሊያ የመሸጉትን አክራሪ ኃይሎችንና አሸባሪዎችን በቁርጠኝነት የታገለችው በዋነኛነት በምን ምክንያት ነው?፣ መከላከያ ሠራዊታችን በሶማሊያ የተሰማራውን የአፍሪካ ህብረት ተልዕኮን ያኔ መቀላቀሉ ያስገኘው ፋይዳ ምንድነው?' የሚሉ ጥያቄዎችን ማንሳት የሚያስፈልግ ይሆናል።

ሠራዊታችን የአገራችንን ሠላምና መረጋጋት እንዲሁም ህገ - መንግሥታዊ ሥርዓቱን በአስተማማኝ እንዲጠብቅ ከተሰጠው ተልዕኮ ባሻገር፤ የጎረቤቶቻችንና የአካባቢያችንን ሠላምና መረጋጋት በማስጠበቅ ረገድ የበኩሉን ድርሻ እንዲጫወት ከተባበሩት መንግሥታትና ከአፍሪካ ህብረት ተደጋጋሚ ጥሪዎች ይቀርቡለታል።

ይህን ተልዕኮ በዓለምና በአህጉር አቀፍ የሠላም ማስከበር ጥበቃዎች በንቃት በመሳተፍ እየተወጣ ነው። በዚህም በዓለም ከፍተኛ ሠራዊት ካሰማሩ አገሮች በርካታ የሠላም አስከባሪ ሠራዊት በማሰማራት ደረጃ ከቀዳሚዎቹ ረድፍ ላይ የሚገኝ ነው። ተልዕኮውም በቁጥር ከፍተኛነት ብቻ የተገደበ ሳይሆን በሱዳን አብዬ ግዛት በብቸኝነት ግዳጁን እያከናወነ ያለ ነው።

ከዚህ በተጨማሪም በተሰማራባቸው ሁሉም ግዳጆች ያለውን ፍፁም ቁርጠኝነት በማሳየቱ ዓለም አቀፍ ግዳጅ የመፈፀም ብቁ አመራርና ዲሲፕሊን ያለው ሠራዊት የያዘ ኃይል ስለሆነም፤ በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ዘንድ "የሠላም አምባሣደር" የሚል ሥያሜን የተቸረ ህዝባዊ ወገንተኝነት ያለው ሠራዊት ነው።

በ2006 ዓ.ም በሶማሊያ የሚገኘውን የአፍሪካ ሠላም አስከባሪ ኃይልን ለማጠናከር የአሚሶምን ተልዕኮ እንዲቀላቀል ለኢትዮጵያ በቀረበላት ጥሪ መሠረት፤ ከአራት ሺህ በላይ የሚሆኑ የመከላከያ ሠራዊታችን አባላት ወደ ሥፍራው ተሰማርተው ቆይተዋል።

ግዳጃቸውንም ቀጣና ሦስትንና አራትን በመረከብ ኃላፊነት በተሞላበት መንፈስ ሲወጡ ቆይተዋል። በነገራችን ላይ ይህ ተጨማሪ ተልዕኮ የሠራዊታችን ቁጥር በሠላም ማስከበር ተልዕኮ ያለውን ተሳትፎ ቁጥር ወደ 12 ሺህ እንዲጠጋ ያደርገዋል። ያም ሆነ ይህ ግን እዚህ ላይ የመከላከያ ሠራዊታችን በሶማሊያ የአፍሪካ ሠላም አስከባሪ ህብረት የሠላም ተልዕኮን መቀላቀሉ የሚኖረውን ፋይዳ ማጤን ተገቢ ይሆናል። ከዚህ በተጨማሪ የአሚሶም ተልዕኮው ከዚሁ ቀደም ከተሳተፈባቸው የሠላም ማስከበር ግዳጆች በምን እንደሚለይ መዳሰስም ተገቢ ይሆናል።

እንደሚታወቀው አገራችን የጀመረችው የፀረ-ድህነት ትግል በተሳካ ሁኔታ እየተፈፀመ ይገኛል። የአገራችንን ህዝቦች ህልውና አደጋ ላይ ጥሎት የኖረው የድህነትና የኋላ ቀርነት ካብ በአገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የነቃ ተሳትፎና ርብርብ መናድ ጀምሯል። ስለሆነም መላው የአገራችን ህዝቦች በዋነኛ ጠላታቸው በሆነው ድህነትና ኋላ ቀርነት ላይ እየተቀዳጁት ያለው ድል ቀጣይነት እንዲኖረው ብሎም ዘላቂ ይሆን ዘንድ፤ በአገራችንና በቀጣናው አስተማማኝ ሠላም መኖሩ ወሣኝ ነው።

የውስጥ ሠላማችንን በህዝቦች ሙሉ ተሳትፎ በማጠናከር የጎረቤቶቻችንንና የአህጉራችንን የሠላም እጦት በጋራ ለመፍታት ኢትዮጵያ ጥረቷን ቀጥላለች። አፍሪካዊ ወንድማማችነት ከምንጊዜውም በላይ ተጠናክሮ ለአካባቢያዊና አህጉራዊ የሠላም ችግሮች መፍትሄ እንዲያመነጭ በማደራደር እና አለመረጋጋት በገጠማቸው አገሮች ውስጥ በተግባር ሠላም አስከባሪ ሠራዊታችንን በተደጋጋሚ በማሰማራት የሚጠበቅባትን ኃላፊነት እየተወጣችም ነው።

ቀደም ሲል ለመግለፅ እንደተሞከረው የሶማሊያ መንግሥትና ህዝቦች በተደጋጋሚ ህልውናቸው በአክራሪ አሸባሪዎች አደጋ ላይ በወደቀበት ወቅትም የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት እነዚህን የጥፋት ኃይሎች ከመደምሰስ ጎን ለጎን፣ ፍፁም ህዝባዊነትን በተላበሰ መንገድ ድጋፍ ሲያደርግ ቆይቷል።

ይህ የመንግሥት በጎ ጥረት፣ በሠራዊታችን ህዝባዊነት፣ የዓላማ ፅናትና ስኬታማ ተልዕኮዎች ታጅቦ በጎረቤቶቻችንና በወዳጆቻችን እንዲሁም በአካባቢያዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ተቋማት ዘንድ ከፍተኛ ተዓማኒነትን እንድታተርፍ አድርጓታል። በመሆኑም የአገራችን የሠላም ጥረት ከምንጊዜውም በላቀ ደረጃ

ተፈላጊነቱ በመጨመር ላይ ይገኛል። ይህም የሠራዊታችንን ብቃትና ጥንካሬ ከማሳየቱም በላይ፤ አገራችን በዓለም አቀፉ መድረክ ያላት ተደማጭነት እያደገ መምጣቱን ያመለክታል።

ታዲያ የአገራችንን የሠላም ማስከበር ሚና እመርታን ስንዳስስ መንግሥት ብሎም የመከላከያ ሠራዊታችን ለህዝቦች ሠላም ያላቸውን ፅኑ እምነት በተደጋጋሚ በተግባር እየገለፁና እውነተኛ የሠላም ኃይል መሆናቸውን ያረጋገጡበት ነው። ሌላው ቀርቶ የቅርብ ጎረቤቶቻችንም ሆኑ የዓለም ህዝቦች ይህን እውነታም በተደጋጋሚ መስክረዋል።

ለዚህ ጥሩ ማሣያ የሚሆነው ሁለቱም ሱዳኖች (ሰሜንና ደቡብ) በአብዬ ግዛት ጉዳይ በአንድ ድምፅ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መከላከያ ሠራዊት ብቻ እንዲሰማራ መፍቀዳቸው፣ ከገባም በኋላም በሁለቱም ወገን ተቀባይነት ያለው ስኬታማ ሥራ መከወን መቻሉን ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል።

ይህም የዓለምን ህዝብ አስደምሟል። መከላከያ ሠራዊታችን በሙሉ አቅሙ ሳይሆን በደጋፊነት ሚና ብቻ ሶማሊያ ውስጥ ባደረገው ጥረት፤ በአገሪቱ ለታዩት አዎንታዊ ለውጦች በርካታ ሶማሊያውያንን አድናቆት ችረውታል። ለዛሬዋ ሶማሊያ እዚህ ደረጃ መገኘት የአብዛኛውን የሶማሊያን ህዝብ ቀልብ ስቧል።

በመሆኑም ይህን የሠራዊታችንን ማንነት ቀደም ባሉት ተልዕኮዎቹ በውል የሚገነዘቡት የሶማሊያ ፌዴራላዊ መንግሥትና ህዝብ፤ 'ለአገራችን ሠላም ትክክለኛ ድጋፍ ማግኘት የምንችለው ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ መከላከያ ሠራዊት ስለሆነ በአሚሶም ውስጥ ይካተትልን' ሲሉ በተደጋጋሚ ጥያቄ ማቅረባቸው የቅርቡ ትዝታ ነው።

ይህም በሁሉም ጎረቤቶቻችን ዘንድ መንግሥት ብሎም የመከላከያ ሠራዊታችን ፅኑ የሠላም ኃይሎች መሆናችንን ብቻ ሳይሆን፣ የጎረቤቶቻቸውን ሠላም ከአገራቸው ሠላም ነጥለው የማያዩ ኃይሎች መሆናቸውን ጭምር ያረጋገጡበት ሃቅ መሆኑ አይታበይም።

ምክንያቱም በተለያዩ ወቅቶች ለአገራችን ለሚቀርቡት የሠላም ማስከበር ጥሪዎች አንድም ቀን እጁ ታጥፎ የማያውቀውና የሠላም ኃይል የሆነው የመከላከያ ሠራዊታችን፤ ዛሬም ከጎረቤት የሶማሊያ ህዝብ የቀረበለትን ጥያቄ ተቀብሎ አሚሶምን ሲቀላቀል፤ ያለፉት ዓመታት የሠላም ማስከበር ልምዶቹንና ብቃቶቹን ቀምሮ ተግባሩን ስለሚያከናውን የአገራችንን መልካም ገፅታ የበለጠ ለመገንባት የላቀ ፋይዳ ስለሚኖረው ነው።

እርግጥ ሠራዊታችን የሠላም አምባሣደር ሆኖ ወደ ጎረቤት ሶማሊያ የአሚሶምን ግዳጅ ተቀብሎ ሲንቀሳቀስ ያነገባቸውን ዋነኛ ተልዕኮዎች ገቢራዊ እያደረገ ይገኛል። እነርሱም በተረከባቸው ቀጣናዎች ያለውን ሠላም አስተማማኝ የማድረግ፣ ከአሚሶም እና በእርሱ ሥር ካሉ የሠላም አስከባሪ ኃይሎች ጋር በመጣመር በሶማሊያ የመሸጉ ሽብርተኞችን መደምሰስና ማጥፋት እንዲሁም ከህዝቡ ጋር በመሆን የተረጋጋ የመስተዳድር መዋቅሮችን እንዲፈጠሩ መሥራት ነበር።

ከዚህ በተጨማሪም በሌሎች የሠላም ማስከበር ተልዕኮዎቹ እንዳደረገው ሁሉ፤ በሶማሊያም ህዝቡ ራሱን የሚያስተዳድርበትንና የፀጥታ መዋቅሩን በባለቤትነት የሚመራበትን ሁኔታ የመፍጠር፣ የሶማሊያ መንግሥትን

የፀጥታ ኃይል የተሻለ ብቃት እንዲኖረው ለማድረግ የማሰልጠን፣ የማስታጠቅ፣ የማደራጀት፣ የራሱንም አቅም እንዲገነባ የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወንም ነው።

ከእነዚህ ተግባራቱ ጎን ለጎንም በተሰጠው ቀጣና ውስጥ ማህበራዊ አገልግሎቶችን የማቀላጠፍና በዚህም ለዕርዳታ ሰጪዎች ምቹ ሁኔታን በመፍጠር የዕለት ደራሽም ሆነ ሌሎች ሰብዓዊ ተግባሮች በተገቢው ሁኔታ እንዲደርሱ ማድረግ፣ መንግሥት በሚደግፈው ውስን ሀብትም ጉልበቱንና እውቀቱን በማስተባበር አንዳንድ ማህበራዊ ተቋማትን ለአካባቢውን ኅብረተሰብ የመገንባት ተልዕኮን ያነገበ ነው።

መከላከያ ሠራዊታችን ከዚህ ቀደም በነበሩ የሠላም ማስከበር ተልዕኮዎች ካካበተው የዳበረ ልምድ በመነሳት ተልዕኮውን በአስተማማኝ እንደሚወጣ ጥርጥር የለውም። ለዚህም ዋነኛው ምክንያት ሠራዊቱ ከሌሎች አገሮች የላቀ ዘመናዊ የጦር መሣሪያ ስለታጠቀ አይደለም — ትጥቁ ህዝባዊነቱ ብቻ ስለሆነ እንጂ። የጎረቤቶቻችን ሠላም የእኛም ጭምር መሆኑንም ስለሚገነዘብ ይህን ህዝባዊ ባህሪውን ተላብሶ ከሌሎች አገራት ኃይሎች ጋር በመሆን ተግባሩን እየተወጣ ነው። የጎረቤቶቻችን ሠላም የእኛም ስለሆነ በፀና ህዝባዊ መሠረት ላይ የቆመው ሠራዊታችን ይህን ተግባሩን በአኩሪ ሁኔታ በመወጣት እስከወዲያኛው የአሸባሪዎችን አንገት የሚያስደፋበት ወቅት ሩቅ አይሆንም።